# ***ቃሉን ማዕከል ያደረገ ሕይወት***

"***ቃሉን ማዕከል ያደረገ ሕይወት***" የሚለውን ርዕስ ለመነጋገር ስንዘጋጅ የእግዚአብሔር ቃል ምንነትን ተናግሮ ማለፍ አስፈላጊ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል (መጽሐፍ ቅዱስ) እግዚአብሔር ራሱን፣ የዘላለም ዓላማውንና ለሰዎች ያለውን ሃሳብ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ለሰው ልጆች የገለጸበት ቃል ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ ሰዎች ይልቁንም ደግሞ በክርስቶስ ደም ተዋጅተው የእግዚአብሔር ልጅነት ስልጣን ያገኙ አማኞች በእግዚአብሔር ቃል ሊተዳደሩና በዚህ ሕያው ቃል ስልጣን ስር ሊገዙ እግዚአብሔር ይጠብቅባቸዋል፡፡ ስለዚህ ቃሉን ማዕከል ስላደረገ ሕይወት መነጋገር ለክርስቲያኖች ወሳኝና አስፈላጊ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም፡፡

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ እንደምንመለከተው እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያዘጋጀው ሕይወት እውን የሚሆነው በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ነው፡፡ ስለዚህ የሰው ሕይወት መጀመርያና መጨረሻ/ፍጻሜ ቃሉን ማዕከል ማድረግ ስላለበት ይህንን ርዕስ ለመነጋገር እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ካለው ዓላማ መጀመርና በዚህ ዓውድ ይህንን ርዕስ መመልከት ጠቃሚ ነው ብየ አስባለሁ፡፡

## I. እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለው ዓላማ ምንድን ነው?

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል አስደናቂ የሆነ እቅድ ማዘጋጀቱን መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ ያደርግልናል፡፡ ይህን አስደናቂ እቅድ ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ተልኮ ወደዚህ ምድር የመጣበትን ዓላማ በገለጸበት በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 10 ቁጥር 10 ላይ ግልጽ አድርጎ አስቀምጦታል፡፡

> *ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም፤ እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ፡፡ (ዮሐ 10፡10)*

ከዚህ ጥቅስ እንደምንመለከተው ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ እግዚአብሔር መልዕክተኛ ወደዚህ ምድር የመጣበት ዓላማ ሁለትዮሽ ገጽታ አለው፡፡ ይህም **ሰዎች ሕይወት እንዲሆንላቸውና የተቀበሉት ሕይወት እንዲበዛላቸው ወይም እንዲትረፈረፍላቸው** ነው፡፡

ጳውሎስ ይህንን እውነት እጅግ በጣም ግልጽ አድርጎ አስቀምጦታል፡፡ ይህን ከሚከተሉት ሁለት ጥቅሶች በሚገባ ማየት ይቻላል፡-

> *በወንጌል አላፍርምና፤ አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው፣ ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ሐይል ለማዳን ነውና፡፡ ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎ እንደተጻፈ የእግዚአብሔር ጽድቅ ከእምነት ወደ እምነት በእርሱ (በወንጌል/በእግዚአብሔር ቃል) ይገለጣልና፡፡ (ሮሜ 1፡16-17)*

ከዚህ እንደምንመለከተው የእግዚአብሔር ዓላማ ሁለትዮሽ ገጽታ እንዳለው ሁሉ፤ የእግዚአብሔር ቃልም (ወንጌል) ሁለትዮሽ ጠቀሜታ እንዳለው መመልከት ይቻላል፡፡ ይህም፡-

(1) ሰዎች ድነት እንዲያገኙ
(2) የዳኑ ሰዎች ደግሞ የእግዚአብሔር ጽድቅ ከእምነት ወደ እምነት በሕይወታቸው እንዲገለጥ ለማድረግ ነው፡፡

*ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና፤ ይህም ጸጋ፤ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊ ምኞትን ክደን የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የምላካችንና የመድሃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፣ ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል፤ (ቲቶ 2፡11-13)*

ከዚህ ጥቅስ ደግሞ ከላይኛው ሀሳብ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ሁለት ነገሮችን እንመለከታለን፡-

(1) የማዳን ሃይል ባለው በወንጌል ምክንያት የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦልናል
(2) ይህ በወንጌል በኩል የተገለጠው የእግዚአብሔር ጸጋ እግዚአብሔርን በመምሰል እንድንኖር የሚያደርግ ጸጋ ነው፡፡

## II. <u>የእግዚአብሔር ቃል ሁለትዮሽ ጠቀሜታ (ጥቅም)</u>

### 1. <u>የእግዚአብሔር ቃል ሰዎች ሕይወት እንዲሆንላቸው ደርጋል።</u>

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ <u>**"ሕይወት እንዲሆንላቸው"**</u> ሲል ሰዎች በእርሱ በማመን ዳግም ልደት እንዲቀበሉ፣ በክርስቶስ የሚገኘውን ሰማያዊ ሕይወት እንዲያገኙ፣ ድነትን እንዲቀበሉ፣ የዘላለም ሕይወት እንዲኖራቸው ማለቱ ነው፡፡ ይህ በሰው ህይወት ውስጥ እውን የሚሆነው በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ነው፡፡

*ሁሉም ከእግዚአብሔር <u>የተማሩ</u> ይሆናሉ ተብሎ በነቢያት ተጽፎአል፤ እንግዲህ ከአብ የሰማ የተማረም ሁሉ <u>ወደ እኔ ይመጣል</u>፡፡ (ዮሐ 6፡45)*

*<u>ዳግመኛ የተወለዳችሁት</u> ከሚጠፋ ዘር አይደለም፥ በሕያውና ለዘላለም በሚኖር <u>በእግዚአብሔር ቃል</u> ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ፡፡ (1 ጴጥ 1፡23)*

*ለፍጥረቱ የበኵራት ዓይነት እንድንሆን <u>በእውነት ቃል</u> አስቦ ወለደን፡፡ (ያዕ 1፡18)*

ከዚህ እንደምንመለከተው የእግዚአብሔር ቃል የዘላለም ሕይወት የሚሰጥ መለኮታዊ ቃል ነው፡፡ ጴጥሮስም ይህንን እውነት በግልጽ መስክሯል፡፡

*ኢየሱስም ለአሥራ ሁለቱ፡- እናንተ ደግሞ ልትሄዱ ትወዳላችሁን? አለ፡፡ ስምዖን ጴጥሮስ፦ ጌታ ሆይ፥ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ <u>የዘላለም ሕይወት ቃል</u> አለህ፤ … ብሎ መለሰለት፡፡ (ዮሐ 6፡67-69)*

ዳግም ልደት (አዲስ ልደት) መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት በአንድ ሰው ህይወት ውስጥ በሚሰራው ቀጥተኛ ስራ የሚከናወን አስደናቂ የሆነ መለኮታዊ ክስተት ነው፡፡ ዳግም ልደት፣ ከእግዚአብሔር መወለድ፣ የእግዚአብሔር ልጅነት ስልጣን መቀበል፣ ድነት ወይም የዘላለም ሕይወት ማግኘት <u>መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ብቻ የሚያከናውነው መለኮታዊ ስራ ነው፡፡</u>

*ኢየሱስም መለሰ፥ እንዲህ ሲል፦ እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገባ አይችልም። (ዮሐ 3፡5)*

*ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው፤ ሥጋ ምንም አይጠቅምም፤ እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው ሕይወትም ነው። (ዮሐ 6፡63)*

ይህ በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት በሰው ሕይወት ውስጥ እውን የሚሆነው አንዱ የክርስቶስ ተልዕኮ ሰዎች ሕይወት ማግኘታቸው ነው።

## 2. የእግዚአብሔር ቃል አማኞች ሕይወት እንዲበዛላቸው (እንዲትረፈረፍላቸው) ያደርጋል።

ይህ ከላይ የተመለከትነው እውነት መሰረታዊ ሆኖ ሳለ ዳግም ከተወለዱ የእግዚአብሔር ልጆች የሚጠበቅ ሌላ ወሳኝ ነገር አለ። ያም ሕይወታቸው መብዛቱና መትረፍረፉ ነው። ይህ ደግሞ ኢየሱስ እንደ እግዚአብሔር መልዕክተኛ ወደዚህ ምድር የመጣበት ሁለተኛው ዓላማ ነው። ይህንን እንደሚከተለው እንመለከተዋለን።

ይህ **"እንዲበዛላቸው (እንዲትረፈረፍላቸው)"** የሚለው ሃሳብ ወይም ንግግር ዳግም የተወለዱ ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ፣ መንፈሳዊ ፍሬ እንዲያፈሩ፣ ክርስቶስን በመመምሰል የእርሱን መልክ እንዲይዙ፣ ከክብር ወደ ክብር እንዲለወጡ፣ ወዘተ የሚል ሃሳብ አለው። የእግዚአብሔር ዓላማና ፍላጎት አማኞች የዘላለም ሕይወትን አግኝተው እንዲቀመጡ ብቻ ሳይሆን ይህንን ሕይወት በሙላት እንዲለማመዱትና እንዲኖሩት ነው። ይህንን የተትረፈረፈ ሕይወት ወይም የሕይወት ሙላት መለማመድ በእግዚአብሔር ቃል ብቻ እውን የሚሆን ነው።

ይህንን ስናስብ ቃሉን ማዕከል ያደረገ ሕይወት ወሳኝነት እንዳለው በጣም ግልጽ ይሆንልናል። መንፈስ ቅዱስ በቃሉ አማካይነት ዳግም ልደት በመስጠት ድነታችንን እውን እንደሚደርግ ሁሉ ያው አንዱ መንፈስ በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ህይወታችንን ይለውጣል።

ስለዚህ ቃሉን ያማከለ ሕይወት በመኖር ወደዚህ የተትረፈረፈ ሕይወት ወይም የሙላት ሕይወት ልንመጣ እንደምንችልና እግዚአብሔርም ለእኛ ያዘጋጀው ህይወት ይህ እንደሆነ ማስተዋል እንድንችል ጥቂት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ለማስረጃነት እንመለከታለን።

### ለመሆኑ ቃሉን ማዕከል ያደረገ ሕይወት በአማኝ ውስጥ የሚያስከትለው ውጤት ምንድን ነው?

### ሀ) ቃሉን ማዕከል ያደረገ ሕይወት ወደ ክርስቶስ ሙላት እንድናድግ ያደርገናል

*እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፤ ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥ (ኤፌሶን 4፡11-13)*

በዚህ ጥቅስ የምንመለከታቸው የአገልግሎት ቢሮዎችና መንፈሳዊ ስጦታዎች በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ ከእግዚአብሔር ቃል አገልግሎት ጋር የተቆራኙ ናቸው። ከዚህ እንደምንረዳው ወደ ክርስቶስ ሙላት መድረስ የምንችለው ቃሉን በመማርና ቃሉ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በሕይወታችን በሚሰራው ስራ ብቻ ነው።

> *እኛም በክርስቶስ ፍጹም የሚሆን ሰውን ሁሉ እናቀርብ ዘንድ ሰውን ሁሉ እየገሠጽን ሰውንም ሁሉ በጥበብ ሁሉ እያስተማርን የምንሰብከው እርሱ ነው። ለዚህም ነገር ደግሞ፥ በእኔ በኃይል እንደሚሠራ እንደ አሠራሩ እየተጋደልሁ፥ እደክማለሁ። (ቆላስይስ 1፡28-29)*

ከዚህ ጥቅስ እንደምንመለከተው ቃሉን ማዕከል ያደረገ ሕይወት ወደ ክርስቶስ ሙላት እንድንደርስ ወይም በክርስቶስ ፍጹም ሆነን ለእግዚአብሔር እንድንቀርብና በአገልግሎታችንም ሌሎችን እንድናቀርብ ያደርጋል።

## ለ) ቃሉን ማዕከል ያደረገ ሕወት እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕይወት እንድንኖር ያደርገናል።

> *ከተወደደ ከእኛም ጋር አብሮ ባሪያ ከሆነው ከኤጳፍራ እንዲህ ተማራችሁ፥ እርሱም ስለ እናንተ ታማኝ የክርስቶስ አገልጋይ ነው። ደግሞም በመንፈስ ስለሚሆን ስለ ፍቅራችሁ አስታወቀን። ስለዚሁ እኛ ደግሞ ይህን ከሰማንበት ቀን ጀምረን የፈቃዱ እውቀት መንፈሳዊ ጥበብንና አእምሮን ሁሉ እንዲሞላባችሁ እየለመንን፥ ስለ እናንተ ጸሎትን አልተውንም። በበጎ ሥራ ሁሉ ፍሬ እያፈራችሁ በእግዚአብሔርም እውቀት እያደጋችሁ፥ ከደስታም ጋር በሁሉ ለመጽናትና ለመታገሥ እንደ ክብሩ ጉልበት መጠን በኃይል ሁሉ እየበረታችሁ፥ በቅዱሳንም ርስት በብርሃን እንድንካፈል ያበቃንን አብን እያመሰገናችሁ፥ በነገር ሁሉ ደስ ልታሰኙ ለጌታ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እንለምናለን። (ቆላስይስ 1፡7-12)*
>
> *በቀረውስ ወንድሞች ሆይ፣ እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት እንዴት መኖር እንደሚገባችሁ አስተምረናችኋል፤ በእርግጥም እንደዚያው እየኖራችሁ ነው። ስለሆነም በጌታ በኢየሱስ የምንለምናችሁና የምንመክራችሁ ከዚህ በበለጠ ሁኔታ በዚሁ እንድትገፉበት ነው። (1ተሰሎንቄ 4፡1)*

እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕይወት መኖር የሚቻለው የእግዚአብሔር ቃል በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በእኛሕይወት ሲሰራ ብቻ ነው።

## ሐ) ቃሉን ማዕከል ያደረገ ሕይወት ከተቀላቀለ (ከዓለማዊነትና ከቅይጥ) ሕይወት እንድንወጣና እንደ ጥሪያችን በቅድስና እንድንኖር ያደርገናል።

> *በእውነትህ ቀድሳቸው፣ ቃልህ እውነት ነው። (ዮሐንስ 17፡17)*
>
> *በጌታ በኢየሱስ የትኛውን ትእዛዝ እንደ ሰጠናችሁ ታውቃላችሁና። ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነውና፤ ከዝሙት እንድትርቁ፥ እግዚአብሔርን እንደማያውቁ አሕዛብ በፍትወት ምኞት አይደለም እንጂ፥ ... ለርኩሰት ሳይሆን እግዚአብሔር በቅድስና ጠርቶናልና። (1ተሰሎንቄ 4፡2-7)*

*ዕዝራ* 7፡10 - "*ዕዝራ የእግዚአብሔርን ሕግ በማጥናትና በማድረግ፣ ለእስራኤልም ስርዓቱንና ሕጉን በማስተማር ራሱን ፈጽሞ ሰጥቶ ነበር።*"
*ነህምያ* 8፡1-3 - *ዕዝራ የሕጉን መጽሐፍ (ቃሉን) ለሕዝቡ አነበበ።*
*ነህምያ* 9፡1-3 - *ሕዝቡ ጾመው፣ ማቅ ለብሰው፣ በራሳቸው ላይ ትቢያ ነስንሰው ከጸለዩና ንስሃ ከገቡ በኋላ ራሳቸውን ከባዕዳን ለዩ።*
*ነህምያ* 10፡28-30 - *ይህንንም ሃጢአት እንዳይደግሙ ቃለ መሐላ (ቃል ኪዳን) ፈጸሙ።*

## *መ) <u>ቃሉን ማዕከል ያደረገ ሕይወት ወደ እውነተኛ አምልኮና ምስጋና እንድንገባ ያደርገናል።</u>*

በሌላ አባባል *ቃሉን ማዕከል ያደረገ ሕይወት* ደስታ፣ ሐሴት የተሞላበት፣ እግዚአብሔርን የማወደስ፣ የማመስገን፣ እርሱን ከፍ ከፍ የማድረግ ህይወት ውስጥ እንድንገባ ያደርገናል።
*ነህምያ* 8፡1-3 - *ዕዝራ የሕጉን መጽሐፍ (ቃሉን) ለሕዝቡ አነበበ።*
*ነህምያ* 8፡5-6 - ህዝቡ ለእግዚአብሔር ስግደት ወይም አምልኮ አቀረበ።
*ነህምያ* 9፡5-6 - ሕዝቡ እግዚአብሔርን አወደሱ፣ አመሰገኑ፣ ከፍ ከፍ አደረጉ።

## *ሠ) <u>ቃሉን ማዕከል ያደረገ ሕይወት የእግዚአብሔርን ቤት እንድንወድ፣ ለእግዚአብሔር ስራ ያለንን እንድንሰጥና በአግባቡ ተሰጥተን በምሳሌነት እንድናገለግል ያደርገናል።</u>*

*ነህምያ* 8፡1-3 - *ዕዝራ የሕጉን መጽሐፍ (ቃሉን) ለሕዝቡ አነበበ።*
*ነህምያ* 10፡36-39 - ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ቤት ስራ በኩራቱን አስራቱን ለመስጠት፤ የአምላቸውንም ቤት ለመንከባከብና ለማገልገል ወሰኑ።

> *ሰዎች ሁሉ የሚያውቁትና የሚያነቡት በልባችን የተጻፈ መልዕክታችን እናንተ ናችሁ። እናንተም በሕያው እግዚአብሔር መንፈስ እንጂ በቀለም አይደለም፣ ሥጋ በሆነ በልብ ጽላት እንጂ በድንጋይ ጽላት ያልተጻፈ፣ በእኛም የተገለገለ የክርስቶስ መልዕክት እንደሆናችሁ የተገለጠ ነው። (2 ቆሮንቶስ 3፡2-3)*

## *ረ) <u>ቃሉን ማዕከል ያደረገ ሕይወት የእግዚአብሔር ሃሳብ በሕይወታችን እንዲከናወንና መንገዳችን እንዲቀናልንና እንዲሳካልን ያደርጋል።</u>*

> *ነገር ግን ጽና፥ እጅግ በርታ ባሪያዬ ሙሴ <u>ያዘዘህን ሕግ ሁሉ ጠብቅ፥</u> አድርገውም በምትሄድበትም ሁሉ <u>እንዲከናወንልህ</u> <u>ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበል</u>። <u>የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፥</u> ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና <u>ታደርግ ዘንድ</u> በቀንም በሌሊትም አስበው የዚያን ጊዜም <u>መንገድህ ይቀናልሃል</u> <u>ይከናወንልሃልም</u>። በምትሄድበት ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና ጽና፥ አይዞህ አትፍራ፥ አትደንግጥ ብዬ አላዘዝሁህምን? (ኢያሱ 1፡7-9)*

እነዚህ ከላይ የዘረዘርናቸው ነገሮች በሙሉ የሕወታችን ሁለንተና ናቸው። የሕይወት መብዛት ወይም መትረፍረፍ እውነተኛው ትርጉም ይኸው ነው። ይህ የበዛ ሕይወት (የተትረፈረፈ ሕይወት) መኖር የምንችለው *ቃሉን ማዕከል ያደረገ ሕይወት* ስንኖር ብቻ ነው።

## III. *ቃሉን ማዕከል ያደረገ ሕወት ለመኖር የመጨከናችን ምልክት ምንድን ነው?*

### 1. *ቃሉ በየትኛውም የሕይወት አቅጣጫችን ባለስልጣንና መመርያ መሆኑን መቀበል*፡፡

የእግዚአብሔር ቃል መለኮታዊ ሥልጣን ያለው ቃል ነው፡፡ ይህንን እውነት ከተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መመልከት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ያህል ግን ጴጥሮስ የሰጠንን ማስገንዘብያ እንመልከት፡-

> *ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፣ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ፡፡ (2 ጴጥሮስ 1፡21)*

ከዚህ የተነሳ አማኞች ይህንን መለኮታዊ ቃል በየትኛውም የሕይወት አቅጣጫቸው፣ በየትኛውም ጊዜና ሁኔታ ስልጣኑንና መመርያነቱን ሊቀበሉ ይገባል፡፡ ይህንን ከሚከተሉት ጥቅሶች በግልጽ ማየት ይቻላል፡፡

> *እኔም ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል <u>በልብህ ያዝ</u>፡፡ ለልጆችህም <u>አስተምረው</u>፥ በቤትህም ስትቀመጥ፥ በመንገድም ስትሄድ፥ ስትተኛም ስትነሳም ተጫወተው፣ በእጅህም <u>ምልክት አድርገህ እሰረው</u> <u>በዓይኖችህም መካከል እንደክታብ ይሁንልህ</u>፡፡ በቤትህም መቃኖች በደጃፍህም በሮች ላይ ጻፈው፡፡ (ዘዳግም 6፡6-9)*
>
> *ሕግህ ለእግሬ መብራት፥ ለመንገዴ ብርሃን ነው፡፡ (መዝ 119፡105)*
>
> *የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል፡፡ (2 ጢሞቴዎስ 3፡16-17)*

### 2. *ቃሉን ለመስማት (ለማንበብ፣ ለማጥናትና ለመረዳት) ራሳችንን ማዘጋጀት (መስጠት)*፡፡

> *ትእዛዝህን አሰላስላለሁ፥ መንገድህንም እፈልጋለሁ፡፡ (መዝ 119፡15)*
> *አቤቱ፥ ሕግህን እንደ ምን እጅግ ወደድሁ! ቀኑን ሁሉ እርሱ ትዝታዬ ነው፡፡ (መዝ 119፡97)*
>
> *ቃልህ ለጕሮሮዬ ጣፋጭ ነው ከማርና ከወለላ ይልቅ ለአፌ ጣፈጠኝ፡፡ (መዝ 119፡103)*
>
> *በፍጹም ልቤ ጮኽሁ፥ አቤቱ፥ ስማኝ ሥርዓትህን እፈልጋለሁ፡፡ (መዝ 119፡145)*

<u>ለሚከተሉት አዲስ ኪዳናዊ ትዕዛዛትም ተገቢ ምላሽ መስጠት ይጠበቅብናል፡፡</u>

> *የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ፡፡ (ቆላስይስ 3፡16)*
>
> *ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እንደ ሆነ፥ ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደ ተወለዱ ሕፃናት ተንኰል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ፡፡ (1 ጴጥሮስ 2፡2-3)*

## <u>*ቃሉን ለመስማት (ለማንበብ፣ ለማጥናትና ለመረዳት) የሚከተሉት ነገሮች ያስፈልጋሉ*</u>

(*ያዕቆብ* 1፡19-21)

### (*ሀ*) <u>*የተከፈተ ጆሮ*</u>

*ስለዚህ፣ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፣ ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ … ይሁን፤ (ያዕቆብ 1፡19ሀ)*

ይህ ***ለመስማት*** የሚለው ቃል የሚያመለክተው ምን እንደሆነ ለማስተዋል ካስፈለገ ዓውዱን መመልከት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ያዕቆብ 1፡21ለ ላይ ስንመለከት ይህ ቃል የሚያመለክተው ***በውስጣችሁ የተተከለውን ቃል*** የሚለውን ነው፡፡ ስለዚህ ቃሉን <u>ለማድመጥ</u> ራሳችንን ማዘጋጀት ይጠበቅብናል፡፡

### (*ለ*) <u>*የተገታ አንደበት*</u>

*ሰው ሁሉ … ለመናገር የዘገየ ይሁን (ያዕቆብ 1፡19ለ)*

በአንድ ወቅት አንድ ወጣት ሶቅራጥስ ወደሚባለው ፈላስፋ በመምጣት ይህንን ፈላስፋ የመናገር ችሎታ (ስጦታ) እንዲያስተምረው ጠየቀው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ወጣት ለሶቅራጥስ ይህንን ጥያቄ ካቀረበለት በኃላ ንግግሩን አላቆመም፡፡ ይልቁንም በማያቋርጥ ንግግር በመታጀብ ሶቅራጥስ ለመናገር ጊዜ ሊያገኝ በማይችልበት ሁኔታ ፋታ አሳጣው፡፡ ወዲያውኑ ሶቅራጥስ እጁን በወጣቱ አንደበት ላይ በመጫን ***አንተ ወጣት፣ ለማስተምርህ ትምህርት ክፍያ ትከፍላለህ፣ ክፍያው ደግሞ ሁለት እጥፍ ይሆናል*** አለው፡፡ ወጣቱም ግራ በመጋባት ***ለምን?*** በማለት ጠየቀው፡፡ ሶቅራጥስም እንዲህ በማለት መለሰለት፡- *እኔ ሁለት ሳይንሶችን አስተምርሃለሁ፡፡ አንዱ፣ <u>አንደበትህን እንዴት እንደምትቆጣጠር</u> ሲሆን <u>ሁለተኛው ደግሞ አንደበትህን እንዴት እንደምትጠቀምበት</u> ነው* አለው፡፡

አንድ ሰው በአንድ ጊዜ ሊናገርና ሊሰማ ወይም ሊያደምጥ አይችልም፡፡ እኛም ብዙ ጊዜ እንደዚህ ወጣት ነን፡፡ ለመሆኑ እግዚአብሔር ቃሉን በልባችን እንዲዘራ ከእርሱ በጥሞና ጸጥ ብለን ለመስማት ምን ያህል ጊዜ እንሰጣለን? የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ወይም ለማድመጥ ከመሞከራችን በፊት አንደበታችንን መቆጣጠር መቻል አለብን፡፡

### (*ሐ*) <u>*የሰከነና የተረጋጋ መንፈስ*</u>

*ሰው ሁሉ … ለቁጣ የዘገየ ይሁን፤ (ያዕቆብ 1፡19ሐ)*

<u>*ለምን?*</u>

*የሰው ቁጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አይሰራምና፡፡ (ያዕቆብ 1፡20)*

የእግዚአብሔር ቃል ዘር ጥላቻና በቀል በተሞላ ልብ ውስጥ ሊበቅልና ስር ሊሰድድ ፈጽሞ አይችልም፡፡ በሕወታችን ውስጥ ለማብብና ለመፍካት እየሞከረ ያለውን የእግዚአብሔርን ቃል አንቆ ከመያዙ በፊት በልባችን ውስጥ ያለውን ቁጣ፣ ጥላቻ፣ መራራነት፣ ቂምና በቀል ማስወገድ አለብን፡፡

(መ) <u>ንጹህ ልብ</u>

ቃሉን ለመስማት በመዘጋጀት ሂደት የመጨረሻው ደረጃ ንጹህ ልብ ነው። ይህንን ለማድረግ ያዕቆብ ሁለት ነገሮችን ማድረግ እንዳለብን ይነግረናል።

> *ስለዚህ ርኩሰትን ሁሉ የክፋትንም ትርፍ አስወግዳችሁ፣ (ያዕቆብ 1፡21ሀ)*

የጆሮ ቆሻሻ ወይም ኩክ ጆሮን እንደሚደፍንና ለመስማት እንደማያስችል ወይም ደንቆሮነትን እንደሚያስከትል ሁሉ፤ በተመሳሳይ መልኩ የሰው ርኩሰትና ክፋት ሰው ለእግዚአብሔር ጆሮ እንዳይኖረውና የእግዚአብሔርን ቃል በአግባቡ እንዳይሰማ ሊያደርገው ይችላል። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት በመዘጋጀት ሂደት ርኩሰትንና ክፋትን ወይም ማንኛውንም ሐጢአታችንን ማስወገድ ይገባናል።

## 3. <u>የእግዚአብሔርን ቃል በየዋህነት መቀበል</u>

የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ራሳችንን ከማዘጋጀት አቅጣጫ ከላይ ዝርዝር ነገሮችን ተነጋግረናል። አሁን ደግሞ ቀጣዩ ነገር የሰማነውን ቃል የማስተናገድ ሂደት ነው። ይህንን እንዴት ማድረግ እንዳለብን ያዕቆብ በሚገባ ግልጽ አድርጎልናል።

> *ነፍሳችሁን ማዳን የሚችለውን በውስጣችሁም የተተከለውን ቃል በየዋህነት ተቀበሉ። (ያዕቆብ 1፡21ለ)*

በዚህ ጥቅስ ውስጥ ሁለት መሰረታዊ ቃላት አሉ። እነዚህም ***<u>የዋህነት</u>*** እና ***<u>ተቀበሉ</u>*** የሚሉት ናቸው። ***<u>የዋህነት</u>*** ትህትናን፣ ጨዋነትን፣ ልበ ክፍትነትንና የሚማርን ልብ ያመለክታል። ይህ ቃል ቅንነትንና ለመማር የተከፈተ ልብን የሚያመለክት ነው። ቃሉን ለማስተናገድ ***<u>የዋህነት</u>*** እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። ከዚህ በኋላ የሚያስፈልገው ተግባራዊ እርምጃ ወይም ድርጊት ነው። ይህ ደግሞ *<u>ተቀበሉ</u>* በሚለው ቃል ግልጽ ተደርጓል። ***<u>ተቀበሉ</u>*** የሚለው ቃል አስተናግዱት፣ ወደ ልባችሁ አስገቡት የሚል ነው። ስለዚህ እውነት ወይም የእግዚአብሔር ቃል ወደ ልባችን በር በመምጣት ሲያንኳኳ የልባችንን በሮች በመክፈት እንደ ታላቅ እንግዳ ተቀባይ ሰው በየዋህነት ልንቀበለው ይገባናል።

## 4. <u>በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የተገለጠልንን መለኮታዊ ቃል ከሕይወታችን ጋር ማዛመድ (ለቃሉ ምላሽ መስጠት)፡፡</u>

ብዙ ክርስቲያኖች ቃሉንና ቃሉ የሚጠይቀውን ተግባር በማፋታት ሕይወት እየተመላለሱ ይገኛሉ። እንዲያውም ከእግዚአብሔር ቃል ጋር መስማማት የእግዚአብሔርን ቃል ከመታዘዝ ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ የሚያስቡ ብዙ ክርስቲያኖች አሉ። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ራሳችንን ከማዘጋጀትና ቃሉን ከመቀበል ባሻገር ሌላ ወሳኝ እርምጃ እንዳለ መጽሐፍ ቅዱሳችን በተለያዩ ክፍሎች በማያወላዳ መንገድ ግልጽ አድርጎ አስቀምጦልናል። ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን ጥቅሶች መመልከት በቂ ነው።

> *ስለዚህ ይህን ቃሌን <u>ሰምቶ የሚያደርገው</u> ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል። (ማቴዎስ 7፡24)*

*ወደ እኔ የሚመጣ ሁሉ ቃሌንም <u>ሰምቶ የሚያደርገው፥</u> ማንን እንዲመስል አሳያችኋለሁ። (ሉቃስ 6፡47)*

*ኢየሱስም ያመኑትን አይሁድ። እናንተ <u>በቃሌ ብትኖሩ</u> በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ። (ዮሐንስ 8፡31)*

በተመሳሳይ መልኩ ያዕቆብ ራሳችንን ለቃሉ ከማዘጋጀትና ቃሉን ከመቀበል አልፈን ለሰማነው ቃል ምላሽ እንድንሰጥ ወይም ቃሉን በተግባር በሕይወታችን እንድንተገብረው (እንድናዛምደው) በአጽንዖት ይመክረናል ደግሞም ያበረታታናል። ይህንን እውነት ***<u>በያዕቆብ 1፡22-27</u>*** ላይ መሰረት በማድረግ እንመለከተዋለን።

**<u>በዚህ ክፍል ውስጥ ተመለከቱትን ሃሳቦች ልብ ብለን እንመልከት፡-</u>**

(ሀ) ***<u>ታላቅ ትዕዛዝ</u>***

*ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ። (ያዕቆብ 1፡22)*

ይህንን ክፍል በማስተዋል ስንመለከተው ሁለት መሰረታዊ ነገሮች አሉ። እነርሱም፡- ***<u>መስማት</u>*** እና ***<u>ማድረግ</u>*** ናቸው። እግዚአብሔር ቃሉን የማያውቁ አድራጊዎችን አይፈልግም፤ በተመሳሳይ መልኩ ቃሉን የሚያውቁ አላድራጊዎችንም (ቃሉን የማያደርጉትንም) አይፈልግም። መስማት (የእግዚአብሔር ቃል እውቀት) እና ቃሉን ማድረግ ሁለት የማይለያዩ ወሳኝ ነገሮች ናቸው።

ቃሉን ሰምተው የማያደርጉት ሰዎች ልክ በኮሌጆች ወይም በዩኒቨርስቲዎች ለእውቀት ብቻ ሲሉ (ኦዲት ለማድረግ) አንድን ኮርስ ከተመዘገቡ ሰዎች ጋር ይመሳሰላሉ። ኮርስ ኦዲት ለማድረግ የሚመዘገቡ ሰዎች ትምህርቱን በሚገባ ይሰማሉ፣ ማስታወሻ በደንብ ይይዛሉ ነገር ግን የቤት ሥራዎችን፣ ሙከራዎችን (ቴስቶችን)፣ ፈተናዎችን፣ የመስክ ስራዎችንና የጽሑፍ ስራዎችን አይሰሩም። በአጭሩ እነዚህ ሰዎች መረጃን ብቻ የሚሰበስቡ እንጂ የተማሩትን በተግባር የሚተረጉሙ ወይም የሚለማመዱ አይደሉም።

ስለዚህ ልክ እንደተመለከትነው ምሳሌ፤ የክርስትናን እምነት ኦዲት የሚያደርጉ ክርስቲያኖች ከክርስትናቸው ጋር በተያያዘ መልኩ ቃሉን ሰምተው የሚያደርጉ ሳይሆኑ ራሳቸውን እያሳቱ እንደሚኖሩ ያዕቆብ ግልጽ አድርጎልናል። እውነተኛ ክርስቲያኖች ግን ለሰሙት ወይም ለተማሩት የእግዚአብሔር ቃል በተግባር ምላሽ በመስጠት ወይም ቃሉን ከሕይወታቸው ጋር በተግባር በማዛመድ ተግባራዊ የክርስትና ሕይወት ይኖራሉ። በዚህም የክርስትናቸውን እርግጠኝነት በሚኖሩት ክርስቲያናዊ ሕይወት ያሳያሉ።

**(ለ) <u>ተጨባጭ ማብራርያ (መግለጫ)</u>**

ያዕቆብ ታላቁን ትዕዛዝ በቁጥር 22 ላይ ካስተላለፈ በኋላ በቁጥር 23-25 ደግሞ ስለ ሁለት የተለያዩ ዓይነት ሰዎች ይናገራል። እነዚህም ***<u>ሰሚዎች</u>*** እና ***<u>አድራጊዎች</u>*** ናቸው።

*ቃሉን የሚሰማ የማያደርገውም ቢኖር የተፈጥሮ ፊቱን በመስተዋት የሚያይን ሰው ይመስላል፤ ራሱን አይቶ ይሄዳልና፣ ወዲያውም እንደ ምን እንደሆነ ይረሳል። ነገር ግን ነፃ የሚያወጣውን ፍጹሙን ሕግ ተመልክቶ የሚጸናበት፣ ስራንም የሚሰራ እንጂ ሰምቶ የሚረሳ ያልሆነው በስራው የተባረከ ይሆናል። (ያዕቆብ 1፡23-25)*

በዚህ ክፍል እንደምንመለከተው የእግዚአብሔር ቃል ከመስተዋት ጋር በንጽጽር ተቀምጦአል፡፡ ነገር ግን ውጫዊ ማንነትን ብቻ ከሚያሳየው መስተዋት ጋር ሲነጻጸር የእግዚአብሔርን ቃል ልዩ የሚያደርገው የሰውን ውስጣዊ ማንነትንና ባህርይን የሚያሳይ መሆኑ ነው፡፡
ይሁን እንጂ ቃሉን ***ሰሚ ብቻ*** የሆነ ነገር ግን የማያደርገው ሰው በፊቱ ያለውን ቆሻሻ በመስተዋት አይቶ ምንም ሳያደርግ እስከ ቆሻሻው እንደሚሄድ ሰው ነው፡፡ ***አድራጊ*** የሆነ ሰው ደግሞ ቃሉን ሰምቶ ለቃሉ ምላሽ የሚሰጥና ቃሉን ከሕይወቱ ጋር የሚያዛምድ ነው፡፡

**(ሐ) <u>ተጨባጭ ተዛምዶ</u>**

ቃሉን ሰምቶ የሚያደርገው ሰው ቃሉን በመታዘዝ ከዚህም የተነሳ እውነተኛ ክርስትና ምን እንደሚመስል የሚያሳይ አንጸባራቂ መስተዋት ይሆናል፡፡ ነገር ግን አንድ ጥያቄ ልንጠይቅ ይገባናል፡፡

<u>አንድ ሰው ቃሉን ሰምቶ የሚያደርግ ለመሆኑ እንዴት ማወቅ እንችላለን?</u>

- <u>በአንድ ሰው ውስጥ በእውነትና በአንደበት መካከል ፍቺ የሌለ ሲሆን፡፡</u>

  *አንደበቱን ሳይገታ ልቡን እያሳተ እግዚአብሔርን የሚያመልክ የሚመስለው ማንም ቢኖር የእርሱ አምልኮ ከንቱ ነው፡፡ (ያዕቆብ 1፡26)*

- <u>በአንድ ሰው ውስጥ በእውነትና የሌሎች ፍላጎትን በማሟላት መካከል ፍቺ የሌለ ሲሆን፡፡</u>

  *ንጹሕ የሆነ ነውርም የሌለበት አምልኮ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ይህ ነው፤ ወላጆች የሌላቸውን ልጆች ባልቴቶችንም በመከራቸው መጠየቅ፣ (ያዕቆብ 1፡27ሀ)*

- <u>በዚህ ሃጢአተኛ ዓለም ውስጥ ስንኖር በአንድ ሰው ውስጥ በእውነትና በክርስቲያናዊ ባህርይ መካከል ፍቺ የሌለ ሲሆን፡፡</u>

  *በዓለምም ከሚገኝ እድፍ ሰውነቱን መጠበቅ ነው፡፡ (ያዕቆብ 1፡27ለ)*

ስለዚህ በአጠቃላይ ቃሉን በመስማትና ቃሉን በተግባር በማድረግ (በመኖር) መካከል ፍቺ ከማካሄድ ልንጠነቀቅ ይገባናል!! እግዚአብሔር ይህንን ፍቺ ይጠላዋል፡፡ ቃሉን ሰምተን ስናደርግ ድነታችንን ክርስቶስን የሚመስል ሕይወት በመኖርና የጽድቅ ፍሬ በማፍራት እንገልጠዋለን፡፡ ቃሉን ማዕከል ያደረገ ሕይወት ደግሞ ይኼ ነው!! ቃሉን ማዕከል ያደረገ ሕይወት የሚኖሩ ክርስቲያኖች ደግሞ ለዓለም ብርሃንና ጨው በመሆን ክርስቶስን ያከብሩታል፡፡

እውነታው እንዲህ ከሆነ፣ ራሳችንን በመለኮታዊ ስልጣን ለሚሰራው ለእግዚአብሔር ቃል ስልጣን በማስገዛት ቃሉን ማዕከል ያደረገ ሕይወት እንኑር፡፡ ያን ጊዜ ቃሉ በእኛ ውስጥ በአስደናቂ ሁኔታ በመስራት ይለውጠናል፡፡ ምክንያቱም የዕብራውያን ጸሐፊ በግልጽ እንዳስቀመጠው፡-

*የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፥ የሚሠራም፥ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፥ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፥ የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል፤ እኛን በሚቆጣጠር በእርሱ ዓይኖች ፊት ሁሉ ነገር የተራቆተና የተገለጠ ነው እንጂ፥ በእርሱ ፊት የተሰወረ ፍጥረት የለም። (ዕብራውያን 4፡12-13)*

ኤርምያስም ስለ መለኮታዊው ቃል ባህርይና ስራ እግዚአብሐር የተናገረውን እንዲህ በማለት በግልጽ አስተላልፎአል፡-

*በውኑ ቃሌ እንደ እሳት፥ ድንጋዩንም እንደሚያደቅቅ መዶሻ አይደለችምን? ይላል እግዚአብሔር። (ኤርምያስ 23፡29)*

<u>**የማስጠንቀቂያ ንግግር**</u>፡-

*እንግዲህ ወደ ዕረፍቱ ለመግባት ተስፋ ገና ቀርቶልን ከሆነ፥ ምናልባት ከእናንተ ማንም የማይበቃ መስሎ እንዳይታይ እንፍራ። ለእነዚያ ደግሞ እንደ ተነገረ ለእኛ የምስራች ተሰብኮልናልና፤ ዳሩ ግን የሰሙት ቃል ከሰሚዎቹ ጋር በእምነት ስላልተዋሐደ አልጠቀማቸውም። (ዕብራውያን 4፡1-2)*

<u>**የልመና ምክር**</u>፡-

*የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፥ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቀናልሃል ይከናወንልሃልም። (ኢያሱ 1፡8)*
*እኔ የምነግርህን የእግዚአብሔርን ቃል፥ እባክህ፥ ስማ፤ይቀናሃል፥ነፍስህም በሕይወት ትኖራለች። (ኤርምያስ 38:20) (ኤርምያስ ለሰዴቅያስ የመከረው ምክር!)*